**በጀርመን ኖርድ ራይን ቬስት ፋለን የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ**

**KINIJIT SUPPORT CHAPTER IN GERMANY (NRW)**


ታህሳስ 6 2000 ዓ.ም.

ቁጥር 14/ቅ.ድ.ኮ

# ቅንጅት ለአምባገነኖች ቦታ የለውም

ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበረባት ኢትዮጵያን ፣ በህላፊነትና በተጠያቂነት ፣ በግልጽነትና በህግ የበላይነትም በማመን የሚሰራ መልካም አስተዳደር ፣ በእኩልነትና በመከባበር ላይ የተመሰረተ አንድነት ያለው ፣ ራሱን ከኋላቀርነትና ድህነት በማውጣት ለእድገትና ብልጽግና አብሮ የሚሰራ ንቁና ኩራት የሚሰማዉ ሕብረተሰብ ለመገንባት የሚፈልግ ፣ በሰላማዊ መንገድ ታግሎ የሚያታግልና ግዙፍ ራዕይ የተሸከመ ደርጅት ነው።

ስለዚህም በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ቅንጅት ለየት ያሉ ባህርያት ያለው ድርጅት ነው። ስለሆነም በሀገር ወስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭ ሀገር የምንኖር ፣ ሀገራችንና ህዝባችንን የምንወድ ዜጎች በኢትዮጵያዊያዊነታችን እንድንደራጅ በቅንጅት ላይም የጸና እምነትና ፍቅር እንዲኖረን በውስጣችን ሰርጾ መግባት የቻለ ድርጀት ነው።

በቅንጅት አመራር አካላት መካከል በማንኛውም ድርጅት ውስጥ ሊፈጠር እንደሚችለው ሁሉ ጥቃቅን የሀሳብ ልዩነቶችና ያለመግባባት ችግሮች እንዳሉ ሲገለፅልን ይሔ በሂደት ሊፈታ የሚችል ፈተና እንደሆነ በመገንዘብ እስካሁን ጠብቀናል። በሰሜን አሜሪካም ሆነ በአውሮፓ በስራ ጉብኝት ላይ ከነበሩት የቅንጅት መሪዎችም እንደተረጋገጠልን የተፈጠሩት ችግሮች እነሱ ወደ ሀገር ቤት ከተመለሱ በኋላ በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ በመከባበር ፣ በዴሞክራሲያዊና በቅንጅት መተዳደርያ ደንብ ላይ በተመረኮዘ ስሌት እንደሚፈቷቸው ነበር።

ነገር ግን ከአንድ ለሐቀኛ ዴሞክራሲ ግንባታ ፣ ለፍትህና የዜጎችን መብት ለማስከበር ቆሚያለሁ ከሚል የአንድ ፓርቲ መሪ ፈፅሞ ሊጠበቅ በማይችል መንገድ በታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ.ም እ.ኢ.ት.እ አቶ ሀይሉ ሻወል በማንአለብኝነትና ጀብደኝነት በስማቸው የተፈረመ መግለጫ አውጥተዋል። በዚህም መግለጫቸው ላይ ባቀረቧቸው መጠነሰፊ በሆኑ ሠንካላና በሓሜት ላይ በተመረኮዙ ምክንያቶች ፣ አሉባልታዎችና መሰረተቢስ ውንጀላዎች ብዙ የቅንጅት ከፍተኛ አመራር ክፍል አባላትን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በቅንጅት ስም እንዳይንቀሳቀሱ አግደዋቸዋል።

አቶ ሀይሉ ሻውል የገዢው ቡድን ከሚያሳየው ለህግ አልገዛም ባይነት በማይተናነስ ሁኔታ ለፈጸሙት ከፍተኛ አውቆ አጥፊነት በድርጅቱ ህገ ደንብ መሰረት የሚገባቸውን ሚዛናዊ ፍርድ እንዲያገኙ አጥብቀን እናሳሰባለን ።

አቶ ሀይሉ ሻውል ቅንጅትን ይወክላሉ ብለን አናምንም። እሳቸው በመሪነት ከሚወክሉት ቡድን ጋር ምንም አይነት ድርጅታዊ ግንኙነት እንደማይኖረን እያሳወቅን አሁንም ቢሆን ቅንጅት የተሸከመዉን ግዙፍ ራእይ በተግባር ለመተርጎም በሃቅ እራስቸዉን ሳይሆን ሀገርንና ወገንን በማስቀደም ሲናገሩ ብቻ ሳይሆን በተግባራቸውም ከምናከብራቸው ፣ ከምንወዳቸው ከሀቀኞቹ የቅንጀት አመራር ክፍል አባላት ጋር በጋራ ለመስራትና አሁንም እንደ ትናንቱ የዜግነት ግዴታችንን ለመወጣት ዝግጁ መሆናችንን እናረጋግጥለን።

**ቅንጅት ፍቅር ነው ፣ ቅንጅት መንፈስ ነው!**

**በጀርመን ሀገር በኖርድ ራይን ቬስት ፋለን ክልል**
**ከቅንጅት ድግፍ ድርጅት የተሰጠ የአቋም መግለጫ**

ታህሳስ 6 2000 ዓ.ም.